ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ሸዕባን 15/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ማርች 18/2022 ግ.

# አደጋዎችን በመቋቋም መከናወን ያለበት ብሄራዊ ትብብር

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{ وَتَعاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى }

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው የአንቀጹዋ ትርጉም፡ (በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡) ማለት ነው፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል፡
የሰለጠኑ ማህበረሰቦች በመተሳሰር፣ በተጋገዝና በመደጋገፍ የታነጹ ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ አደጋዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እነዚህን የተከበሩ ማህበረሰቦች ሲገልጹ እንድህ ይላሉ፡ (በመዋደድቸው፣ በመተዛዘናቸውና በመደጋገፋቸው የምእምናን ምሳሌ ከሱ አንድ አካል በታመመ ጊዜ ሌሎቹም አካላት እንቅልፍ በማጣትና በህመም እንደሚጋሩት የአንድ ሰውነት አካል ነው)፡፡

እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሙእሚን ለሌላው ሙእሚን ከፊሉ ከፊሉን እንሚያጠናክር የካብ ድንጋይ ነው፡፡ ጣቶቻቸውንም አጠላለፉ)፡፡

የአደጋዎች ደንብ በርካታ ጉዳዮችን መሰረት ያደረገ ሀገራዊ ትብብርን ይጠይቃል፡፡ ከነሱም መካከል በመጀመሪያ የሚጠቀሰው ከማንኛውም ማጭበርብር፣ ለበለጠ ትርፍ ሸቀጦችን ከመደበቅና ከብዝበዛ መራቅ የሚለው ነው፡፡ ቀጥተኛው ሃይማታችን እነዚህን አሉታዊ ተግባራት እንዳንፈጽም በጥብቅ ይከልክለናል፡፡ ማንኛውንም የማጭበርበር ተግባር ለመከልከል በመዲና መጀመሪያ ከወረዱ የቅዱስ ቁርኣን አንቀጾች መካከል የሚከተሉት ነበሩ፡

لِلْمُطَفِّفِينَ*الَّذِينَ إِذَا اكْتَالُوا عَلَى النَّاسِ يَسْتَوْفُونَ*وَإِذَا كَالُوهُمْ أَوْ وَزَنُوهُمْ يُخْسِرُونَ*أَلَا يَظُنُّ أُولَئِكَ أَنَّهُمْ مَبْعُوثُونَ* لِيَوْمٍ عَظِيمٍ * يَوْمَ يَقُومُ النَّاسُ لِرَبِّ الْعَالَمِينَ }

(ለሰላቢዎች ወዮላቸው፡፡ ለእነዚያ ከሰዎች ባስሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ፡፡ ለእነርሱም (ለሰዎቹ) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎድሉ (ለኾኑት)፡፡እነዚያ እነርሱ ተቀስቃሾች መኾናቸውን አያውቁምን? በታላቁ ቀን፡፡ ሰዎች ሁሉ ለዓለማት ጌታ (ፍርድ)፤ በሚቆሙበት ቀን (ተቀስቃሾች መኾናቸውን)፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በነብዩ ሹዓይብ (ዐ.ሰ.) ልሳን እንድህ ይላል፡

{وَيَا قَوْمِ أَوْفُوا الْمِكْيَالَ وَالْمِيزَانَ بِالْقِسْطِ وَلَا تَبْخَسُوا النَّاسَ أَشْيَاءَهُمْ وَلَا تَعْثَوْا فِي الأَرْضِ مُفْسِدِينَ}

(«ሕዝቦቼም ሆይ! ስፍርንና ሚዛንን በትክክል ሙሉ፡፡ ሰዎችንም ምንም ነገራቸውን አታጉድሉባቸው፡፡ በምድርም ውስጥ አጥፊዎች ሆናችሁ አታበላሹ፡፡)

እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የሚያታለን ሰው ከኛ ወገን አይደለም)፡፡

ቅን ሃይማኖታችን ማንኛውንም የሸቀጥ መደበቅና ብዝበዛን ከልክሏል፡፡ ይህውም ሰዎችን በማስቸገርና በማሰቃየት ህገ ወጥ ትርፍ ለማግኘት የሰወችን ቀለብና የህይወታቸውን መዋቅር ለአደጋ ስለሚዳርግ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.) እንድህ ይላሉ፡

{يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لاَ تَأْكُلُوا أَمْوَالَكُمْ بَيْنَكُمْ بِالْبَاطِلِ إِلاَّ أَنْ تَكُونَ تِجَارَةً عَنْ تَرَاضٍ مِنْكُمْ وَلاَ تَقْتُلُوا أَنْفُسَكُمْ إِنَّ اللَّهَ كَانَ بِكُمْ رَحِيمًا}

(እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ፡፡ ግን ከእናንተ በመዋደድ የኾነችውን ንግድ (ብሉ)፡፡ ነፍሶቻችሁንም አትግደሉ፡፡ አላህ ለእናንተ አዛኝ ነውና፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (የማንኛውም ሙስሊም ደም፣ ንብረትና ክብር በሙሰሊም ላይ እርም ነው)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (የተሳሳተ ሰው ካልሆነ በስተቀር ለበለጠ ትርፍ ሸቀጦችን የሚደብቅ ሰው የለም)፡፡ ለበለጠ ትርፍ ሸቀጦችን የሚደብቅ ክብርህም ሆነ ህገራዊ ስሜት የለውም፡፡ ምክንያቱም ራስ ወዳድነቱን ከሃይማኖታዊ፣ ሀገራዊና ሰብአዊ ግምት በላይ አድርገዓልና፡፡ በመሆኑም የአላህን ቁጣና የሰዎችን ጥላቻ አትርፏል፡፡

ይህ ለበለጠ ትርፍ ሸቀጦችን የሚደብቅና ወገኖችን የሚበዘብዝ ሰው በመደበቅና በመበዝበዝ የሚያተርፈው ገንዘብ በትንሳኤ ቀን በራሱ ላይ መከራ የሚያመጣበት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ ይህ ግንዛቤው ከዚያ መሰል በደል እንድታቀብ ባደረገው ነበር፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَمَنْ يَغْلُلْ يَأْتِ بِمَا غَلَّ يَوْمَ الْقِيَامَةِ}

(ሰለባንም የሚደብቅ ሰው በትንሣኤ ቀን በደበቀው ነገር (ተሸክሞ) ይመጣል፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሸቀጥ የሚያመጣ ሲሳይ የሚሰጥ ነው፡፡ ሸቀጥ የሚደበቅ ደግሞ የተረገመ ነው)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ብለዋል፡ (የወርቅ ገንዘብና የብር ገንዘብ ተገዢ የሆነ ሰው በጭንቅ ውስጥ ይኖራል)፡፡

ሀገር ወዳድ የሆነ እውነተኛ ነጋዴ ያ የማያምታታ፣ የማያጭበረብርና የማያታለል ነጋዴ ነው፡፡ ይልቁንም ሀገር ወዳድነቱ በተለይም በአደጋዎች ጊዜ በሰዎች ላይ የደረሰውን ችግር ለማቃለል ትርፉን ዝቅ እንዲያደርግ ያስገድደዋል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ተግባር ከአላህ ዘንድ ምንዳ የሚያስገኝ መተዛዘንና አላህ (ዐ.ወ.) በነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ልሳን እውነተኛ ነጋዴ ታላቅ ምንዳ አለው ሲል የገባውን ቃል በግልጽ የሚያሳይ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ታማኝ እውነተኛ ነጋዴ ከነብያት፣ ከጻድቃንና ሰማእታት ጋር ይሆናል)፡፡እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ሲሸጥ፣ ሲገዛና ሲፋረድ ገራገር የሆነን ሰው አላህ ይዘንለት)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የአደጋ ጊዚያት ራስን መውድና ብዝበዛን ሳይሆን ሌላውን ማስቀደምን ይጠይቃል፡፡ ጭካኔና ለኔ ለኔ ማለትን ሳይሆን መተዛዘንን ይጠይቃል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በጎኑ ያለው ጎረቤቱ መራቡን እያወቀ ጠግቦ ያደረ ሰው በኔ አላመነም፡፡) እንድሁም በዚህን ጊዜ መተዛዘን፣ ልግሳናና ስጦታ አስፈላጊ ይሆናሉ፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.) እንድህ ይላል፡

{ وَيُؤْثِرُونَ عَلَى أَنفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِ فَأُولَئِكَ هُمُ الْمُفْلِحُونَ}

(በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ፡፡ የነፍሱንም ንፍገት የሚጠበቅ ሰው እነዚያ እነሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው፡፡) እንድሁም ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (አሽዓሪያዎችኮ በጦርነት ጊዜ ስንቃቸው ሲመናመን እንድሁም በመዲና የልጆቻቸው ቀለብ ሲቀንስ ያላቸውን ሁሉ በአንድ ጨርቅ ያከማቹና እንደገና በመለኪያ እኩል ይካፈሉታል፡፡ እነሱ ከኔ ወገን ናቸው እኔም የነሱ ወገን ነኝ)፡፡

መደጋገፍ የማህበራዊና የሰብኣዊ ትስስርን በማጠናከር እንድሁም ከማህበሩ አባላት መካከል መግባባትንና ፍቅርን በማስፋፋት ታላቅ ሚና የሚጫወት መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ በመሆኑም ቅኑ ሃይማኖታችን እንዲንፈጽመው ይገፋፋናል፡፡ አላህ (ሱ.ዐ.) እንድህ ይላል፡

{ وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ}

(በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡) የዚህ ዓይነቱ መደጋገፍና መተባበር በሌሎቹም የመልካም ሥራ መስኮች በመሰማራት በተለይም ምግብ በማብላትና የደሃዎችን ጉዳይ በማውጣት ጎልቶ ይታያል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) የመልካም ሰሪ ፈሪሃ አላህ ባሮችን ባሕርይ እንድህ በማለት ይገልጸዋል፡

{ وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَى حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا* إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لاَ نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَاءً وَلاَ شُكُورًا إِنَّا نَخَافُ مِن رَّبِّنَا يَوْمًا عَبُوسًا قَمْطَرِيرًا * فَوَقَاهُمُ اللَّهُ شَرَّ ذَلِكَ الْيَوم وَلَقَّاهُمْ نَضْرَةً وَسُرُورًا* وَجَزَاهُمْ بِمَا صَبَرُوا جَنَّةً وَحَرِيرًا }

(ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ «የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡ «እኛ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱ ቀን ከጌታችን እንፈራለንና፤» (ይላሉ)፡፡አላህም የዚያን ቀን ክፋት ጠበቃቸው፡፡ (ፊታቸው) ማማርንና መደሰትንም ገጠማቸው፡፡ በመታገሣቸውም ገነትንና የሐር ልብስን መነዳቸው፡፡) አላህ (ሱ.ወ.) የቀኝ ጓዶችን ሲገልጽ እንድህ ይላል፡

{أَوْ إِطْعَامٌ فِى يَوْمٍ ذِي مَسْغَبَةٍ* يَتِيمًا ذَا مَقْرَبَةٍ* أَوْ مِسْكِينًا ذَا مَتْرَبَةٍ}

(ወይም የረኃብ ባለቤት በኾነ ቀን ማብላት፡፡ የዝምድና ባለቤት የኾነን የቲም፤ ወይም የዐፈር ባለቤት የኾነን ድኻ (ማብላት ነው)፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ደግሞ እንድህ ይላሉ፡ (ምግብን አብሉ፡፡ ዝምዲናንም ቀጥሉ፡፡ ሌሊት ሰዎች በሚተኙበት ወቅት ስግደትን ስገዱ፡፡ ይህን ካደረጋችሁ በሰላም ጀነት ትገባላችሁ)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (ከናንተ በላጫችሁ ምግብን ያበላ ሰው ነው)፡፡

ጌታችን ሆይ ግብጽ ሀጋራችንና ሌሎችንም የዓለም ሀገራት ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሚን፡፡